amhara

# ሴቶች ልጆቻችንን ከግርዛት እንከላከል

IHMIS OIKEUS LIITTO

## የሴቶች ግርዛት ምንድን ማለት ነው?

የሴቶች ግርዛት ማለት፤ ማንኛውም በህክምና ባልተደገፈ መልኩ የሴቶችን ብልት የዉስጥ ወይም የውጪውን ክፍል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ወይም በማንኛውም መልኩ ጉዳት ማድረስ ማለት ነው።

ሴቶችን የመግረዝ ልማድ የማናቸውም ሀይማኖት የማያዘው የቆየ ጥንታዊ ባህል ነው።

## የሴቶች መገረዝ ምን አይነት የጤና ችግር ያስክትላል?

ሁሉም ዐይነት የሴት ልጆች ግርዛት ለጤና በጣም ጎጂ ናቸው። ከግርዛት በኋላ ተከትሎ የሚከሰት የማይቆም የደም መፍሰስ፤ ይህንንም ተከትሎ መመረዝና እስከ ሞት የሚያደርስ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። በዘላቂንት የሚያስክትለውም ጉዳት እንደ ወር አበባ ጊዜ ህመም፣ የመሽናት ችግር፣ መመረዝ፣ የወሊድ ጊዜ መሰንጠቅንና የወሊድ ጊዜ ውስብስብ ችግሮች ይጠቀሳሉ።

# ሴቶችንና ልጃገረዶችን መግረዝም ሆነ ማስገረዝ በፊንላንድ ህግ የተከለከለ ነው።

በተባበሩት መንግስታት ስምምነቶች ውስጥም ግርዛት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መሆኑ ተረጋግጧል። ማንኛውም ዓይነት ግርዛት በፊንላንድ ህግ የተከለከለ ነው። ይህንን ህግ የጣሰና የተላለፈ ማንኛውም ግለሰብ አስር አመታት በሚደርስ ጽኑ እስራት ሊያስቀጣ ይችላል።

በፊንላንድ ነዋሪ የሆነችን ልጅ ለመግረዝ፤ ድርጊቱ ክልክል ወደ ሆነበትም ይሁን ወደ አልሆነበት ሃገር ወስዶ መግረዝ፣ ማስገረዝ ወይም ይህ እንዲፈጸም መርዳት በህግ የሚያስቀጣ ሲሆን፤ ይህም እንዳይፈጸም ወላጅ ወይም በህግ የአሳዳጊነት በብት የተሰጠው ግለሰብ ልጆቹን ከግርዛት የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት።

**ከፊንላንድ ውጪ ከመጓዝዎ በፊት ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገዎ ከዚህ በታች በሚገኘው አድራሻ ማግኘት ይችላሉ።**

ሰሎሜ ተሾመ Solomie Teshome (ቋንቋ: በአማርኛ፤ በእንግሊዝኛ እና በፊንላንድ)
Email: solomie.teshome@ihmisoikeusliitto.fi tel. +358 44 742 0411

IHMISOIKEUSLIITTO

TUETTU VEIKKAUKSEN TUOTOILLA

OIKEUSMINISTERIÖ
JUSTITIEMINISTERIET

Sisäministeriö
Inrikesministeriet

SOSIAALI- JA TERVEYSMINISTERIÖ

Terveyden ja
hyvinvoinnin laitos

Ulkoministeriö
Utrikesministeriet